የኢትዮጵያ ሂሳብ አዋቂዎችና አዲተሮች ማህበር

Tel. +251-11-869-78-60

Ethiopian Professional Association of Accountants & Auditors (EPAAA)

P.O.Box 62757
E-mail epaaa@ethionet.et
Addis Ababa Ethiopia

ቀን፡- መጋቢት-25-2017 ዓ.ም.

ቁጥር፡- ኢ/ሃ/አ/አ/ማ/0098/2017

ለ፡ አዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ
አዲስ አበባ

ጉዳዩ ፡-

1. **መረጃ እና ማስረጃ እንዲሰጠን ስለመጠየቅ፤**
2. **ቅሬታን ስለመግለጽ እና**
3. **ቢሮው በሚዲያ ያስተላለፈውን መልእክት ማስተባበያ እንዲሰጥበት እና መልእክቱን እንዲሰርዝ ስለመጠየቅ።**

የኢትዮጵያ የሂሳብ አዋቂዎችና አዲተሮች ማኅበር **ከ 50 አመት** በላይ ያሰቆጠረ፣ በአፍሪካ የመጀመሪያው የአካውንታንቶች የሙያ ማህበር እና **(PAFA)** የፓን አፍሪካ ፌዴሬሽን ኦፍ አካውንታንትስ ማህበር መስራች የሆነ አንጋፋ የሙያ ማህበር ሲሆን፣ በአሁኑ ሰአት ከ1,500 በላይ የሚሆኑ የሂሳብ እና የኦዲት ሙያ አገልግሎት የሚሰጡ፣ እንዲሁም ተባባሪ አባላት አሉት።

ማህበሩ የተመሰረተበት ዋና አላማም የአባላቱን መብት እና ጥቅም ከማስጠበቅ ጎን ለጎን፣ የአባላቱን የሙያ ስነምግባር መቆጣጠር፣ አባላቱ ሙያቸውን እንዲያሳድጉ ተከታታይ የሙያ ማጎልበቻ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ ሙያውና ባለሙያዎቹ የህዝብ ጥቅምን እንዲያስጠብቁ በማስቻል፣ ለመከታተልና ተገቢ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ ነው።

ቢሮአቹ፣ **"የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ መጋቢት 23 / 2017 ዓ.ም በተለያዩ ሚዲያዎች ከ10 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ በማሳነስና በመሰወር የሂሳብ መዝገቦችን በማዘጋጀት ባቀረቡ የሂሳብ ባለሙያዎችና አዲተሮች ላይ ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፈቃድ ስረዛ እርምጃ እንዲወሰድ የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና አዲት ቦርድን (AABE) መጠየቁን አሳወቀ"** የሚል ዜና በተለያዩ ሚዲያዎች ማሰራጨቱን ተከትሎ፣ ማህበራችን በተሰራጨው ዜና ላይ አስቸኳይ የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ በማድረግ ከላይ በጉዳዩ ላይ በዘረዘርናቸው ሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያለንን ምልከታ እና የማህበራችንን አቋም እንደሚከተለው እንገልጻለን፡-

1. በሂሳብ ባለሙያዎችና አዲተሮች ላይ የተጠየቀውን አስተዳደራዊ ቅጣት አስመልክቶ መረጃ እና ማስረጃ እነዲሰጠን ስለመጠየቅ፤

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በሂሳብ እና አዲት ባለሙያዎች ላይ ከጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፈቃድ ስረዛ የሚደርስ እርምጃ እንዲወሰድ፣ የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና አዲት ቦርድን መጠየቁን አስመልክቶ፣ ቢሮው ህግን ተከትሎ ጥያቄውን እስካቀረበ ድረስ ማህበራችን ምንም አይነት ቅሬታ የለውም፣ እንደውም፣ ቢሮው ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና አዲት ቦርድ (AABE) ያቀረበው ጥያቄ ህጋዊና በታክስ አስተዳደር ***አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 48 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ)*** ለይ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በህግ የተሰጠውን ሀላፊነት እንደተወጣ እናምለን።

በመሰረቱ በንግድ ህጋችንም ሆነ **AABE** በተቀበለው የአለም አቀፍ የሂሳብና የአዲት ደረጃዎች፣ የሂሳብ ሪፖርት የማዘጋጀትና ለሚመለከተው አካል የማቅረብ ሀላፊነት ሙሉ በሙሉ የድርጅቱና ድርጅቱን የሚመሩ የማኔጅመንቶች ሀላፊነት መሆኑ ይታወቃል። በዚህ ላይ የሂሳብ ባለሙያዎች ሀላፊነት ድርጀቱ ያቀረበላቸውን የሂሳብ እና ተያያዥ ሰነዶች ብቻ እና ብቻ በመጠቀም **AABE** በተቀበለው አለም አቀፍ የሂሳብ ደረጃዎችን በሚከተል የሂሳብ ሪፖርቶችን ማዘጋጀት ሲሆን፣ የውጭ አዲተሮች ሀላፊነት ደግሞ በድርጅቱ ተዘጋጅተው የቀረቡ የሂሳብ ሪፖርቶች፣ **AABE** የተቀበለውን አለም አቀፍ የሂሳብ ደረጃዎችን ተከትለው መዘጋጀት አለመዘጋጀታቸውን፣ አለም አቀፍ የአዲት ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ ምርመራ የማድረግና የአዲት ሪፖርት (Audit Opinion) መስጠት ነው።

ስለዚህ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ባለሙያዎቹ ገቢን በማሳነስና በመሰወር የሂሳብ መዝገቦችን ሲያዘጋጁ ደርሼባቸዋለው በማለት በባለሙያዎቹ ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲሰጥ ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና አዲት ቦርድ (AABE) ያቀረበውን ጥያቄ አስመልክቶ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ፣ ማብራሪያ፤ መረጃና እና ማስረጃ እንዲሰጠን በትህትና እንጠይቃለን፡-

1.1. በቢሮአቹ ባደረጋቸሁት ቅድመ አዲት፣ ባለሙያዎቹ የድርጅቱን ሂሳቡ በሚዘጋጁበት ወይም አዲት በሚያደርጉበት ጊዜ ከሪፖርት አቅራቢው የተረከቡትን የሂሳብና ተያያዥ ሰኖዶችን እንደሰወሩትና እና ገቢን ሆነ ብለው ማሳነሳቸውን በምን አይነት መንድ አረጋገጣቹ ?፣

1.2. በቢሮአቹ ባደረጋቸሁት ቅድመ አዲት፣ ተሰወሩ የተባሉትና ገቢን ያሳነሱ ሰነዶች ሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ለባለሙያዎቹ አቅርቦላቸው ሳለ ባለሙያዎቹ ሆነ ብለው ሰነዶቹን በመደበቅ ማሳነሳቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ እና ማስረጃ አላቹ ወይ ?፣ ወይስ ቀድሞውኑ ተሰወሩ የተባሉት, ገቢን ያሳነሱ ሰነዶች ለባለሞያዎቹ ያልቀረቡ ሰነዶች ናቸው ? ፣

1.3. ተሰወሩ የተባሉት፣ ገቢን ያሳነሱ ሰነዶች ለባለሙያዎቹ በሪፖርት አቅራቢው ድርጅት አማካኝነት ቀርቦላቸው ነበር ወይ ?፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ባለሙያዎቹ ተጠይቀው ነበር ወይ ?፣ የባለሙያዎቹ ምላሽ ምን ነበር ?፣

1.4. ተሰወሩ የተባሉት፣ ገቢን ያሳነሱ ሰነዶች ሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ለባለሙያዎቹ ሂሳቡን በሚያዘጋጁበት ወይም አዲት በሚያደርጉበት ወቅት ካላቀረበላቸው፣ በዚህ ላይ የባለሙያዎቹ ሀላፊነት ምን መሆን ነበረበት ?፣ ባልቀረበላቸው ሰነዶች ላይ ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ አግባብ አለ ወይ ?፣

1.5. በታክስ አስተዳደር **አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 48 U)** ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የታክስ ስወራ ተፈጸመ የሚባለው ባለሙያዎች ***"ታክስ ከፋዩ ታክስን ለማሳነስ ወይም ታክሱን ለመሰወር እንዲችል የረዳ፣ ያበረታታ፣ የመከረ እንደሆነ"*** ነው በሚል ተቀምጧል፣ በመሆኑም፣ ባለሙያው ታክስ ስወራን መርዳቱን፣ ማበራታቱን እና መምከሩን ባደረጋችሁት ቅድመ አዲት አረጋግጣቹሀል ወይ ?፣ ወይስ በሌላ ዘዴ ነው ያረጋገጣችሁት ?፣

1.6. በታክስ አስተዳደር **አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 48 ለ)** ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የታክስ ስወራ ተፈጸመ የሚባለው ባለሙያዎች ***"ታክስ ለማሳነስ ወይም የታክስ ስወራን በሚያስከትል መልኩ በማንኛውም መንገድ እያወቀ ከታክስ ከፋዩ ጋር ከተባበረ ወይም የድርጊቱ አጋር ከሆነ"*** ነው በሚል ተቀምጧል፣ በመሆኑም፣ ባለሙያው ታክስ ለማሳነስ እያወቁ ከታክስ ከፋዩ ጋር መተባበሩን፣ የድርጊቱ አጋር መሆኑን ባደረጋችሁት ቅድመ አዲት አረጋግጣቹሀል ወይ ?፣ ወይስ በሌላ ዘዴ ነው ያረጋገጣችሁት ?፣

1.7. ተገኘ የተባለው ከ10.6 ቢሊዮን ሊደበቅ የነበረ ገቢ፣ በምን አይነት ዘዴ ነው የተገኘው ?፣ ይህ ገቢ የተገኘው ተሰወሩ የተባሉት፣ ገቢን ያሳነሱ ሰነዶች ሪፖርት አቅራቢው ድርጅት መጀመሪያ ባቀረበው የሂሳብ መግለጫ ላይ ተደምረው ነው ?፣ ወይስ ሪፖርት አቅራቢው ያቀረበው የሂሳብ መግለጫ ውድቅ ሆኖ በቁርጥ ግብር ተሰልቶ ነው ?፣

1.8. ቢሮአቹ የሂሳብ መዝገብ ውድቅ የሚያደርግበት አግባብ **AABE** የተቀበለውን የአለም አቀፍ የሂሳብና የኦዲት ደረጃዎች ባለሟሟላታቸው ነው ?፣ ወይስ በታክስ ህጎችና መመሪያዎች ላይ በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሰረት ነው ?፣

1.9. በታክስ ህጎችና መመሪያዎች ላይ በተደነገጉ ድንጋጌዎች መሰረት ከሆነ የሂሳብ መዝገቦቹ ውድቅ የሚደረጉት፣ በዚህ ላይ የባለሙያዎቹ ሀላፊነት ምን መሆን ነበረበት ?፣ በዚህ አግባብ የሂሳብ መዝገቦቹ ውድቅ በመደረጋቸው ባለሙያዎቹ ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ አግባብ አለ ወይ ?፣

1.10. ተገኘ የተባለው ከ10.6 ቢሊዮን ሊደበቅ የነበረ ገቢ የተገኘው በሪፖርት አቅራቢው ድርጅት የባንክ የጥሬ ብር ሂሳብ እና ባቀረበው የሂሳብ መግለጫ ላይ በተመዘገበው የ ጥሬ ብር ባላንስ በተፈጠረ ልዩነት ላይ ተመስርቶ ነው ወይ?፣

ልዩነቱን ለማግኘት የባንክ የሂሳብ መግለጫ የሚሳየውን የባንክ ስቴትመንት መረጃ፣ ሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ነው መረጃውን የሰጣቹ ወይስ በህግ በተሰጣቹ ስልጣን መሰረት ከሁሉም ባንኮች በደብዳቤ ተይቃቹ ነው የባንክ ስቴትመንት መረጃውን ያገኛችሁት ?፣ በዚህ ረገድ ባለሙያዎች ከሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ያልተሰጣቸውን የባንክ ስቴትመንት ከሁሉም ባንኮች ደብዳቤ ጽፈው መረጃውን የማግኘት ስልጣን አላቸው ወይ ?፣ ስልጣን ከሌላቸው በዚህ ረገድ ለሚፈጠሩ ችግሮች ባለሙያዎቹ ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ አግባብ አለ ወይ ?፣ በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት ድርጊቱ ታክስ ማጭበርበር ወይም ታክስ ስወራ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል ወይ ?፣ ከሆነ በሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ላይ የወሰዳችሁት እርምጃ አለ ወይ ?፣

1.11. ተገኘ የተባለው ከ10.6 ቢሊዮን ሊደበቅ የነበረ ገቢ የተገኘው ሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ያቀረበው የሽያጭ መጠንና ቢሮአቹ የሽያጭ መጠንን የምወስነው አሁን ባለው የገበያ ዋጋ ነው ብሎ የሪፖርት አቅራቢውን ድርጅት የሽያጭ መጠን በገበያ ዋጋ በመወሰኑ ምክንያት በተፈጠረ ልዩነት ላይ ተመስርቶ ነው ወይ ?፣ በዚህ ረገድ ባለሙያዎች ከሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ከቀረበላቸው የሽያጭ ሰነድ ውጭ በገበያ ዋጋ የመወሰን ስልጣን አላቸው ወይ ?፣ ስልጣን ከሌላቸው በዚህ ረገድ ለሚፈጠሩ ችግሮች ባለሙያዎቹ ተጠያቂ የሚሆኑበት የህግ አግባብ አለ ወይ ?፣ በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት ድርጊቱ ታክስ ማጭበርበር ወይም ታክስ ስወራ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል ወይ ?፣ ከሆነ በሪፖርት አቅራቢው ድርጅት ላይ የወሰዳችሁት እርምጃ አለ ወይ ?፣

1.12. ለዚህ ውሳኔ ያበቃቹ ሌሎች ምክንያቶች፣ መረጃዎችና ማስረጃዎች ካሉ፣ እነዲብራራልን፣ መረጃዎቹና ማስረጃዎቹ እንዲሰጠን እንጠይቃለን::

ከላይ የተጠቀሱትን ማብራሪያዎች፣ መረጃዎችና ማስረጃዎች ማህበሩ የጠየቀበት ዋና ምክንያት፣ በባለሙያዎቹ ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲሰጥ ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና አዲት ቦርድ (AABE) በናንተ በኩል የቀረበው ጥያቄ ተገቢ መሆን አለመሆኑን በማረጋገጥ፣ ባለሙያዎቹ ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ በማህበራችን የባለሙያዎች የስነምግባር መመሪያ መሰረት አስፈላጊወን የቅጣት ውሳኔ ለማሳለፍ እንዲረዳንና በናንተ በኩል የቀረበው ጥያቄ ተገቢ ካልሆነ በቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለብን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርደ ባለሙያዎችን በመወከል ከናንተ ጋር በመመካከር በግብር አሰባሰቡ ስራ ላይ ባለሙያዎች በቅንነትና በታማኝነት እንዲሁም ሙያዊ ስነምግባርን በተላበሰ መልኩ ሙያዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ነው::

2. **<u>በሂሳብ እና ኦዲት ባለሙያዎች ላይ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲወሰን ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (AABE) ያስገባችሁትን ጥያቄ አስመልክቶ በሚዲያ በማስተላለፋቹ በሙያውና በባለሙያዎች ላይ የደረሰውን ሙያዊ ኪሳራ እና በድርጊቱ የተሰማንን ቅሬታ ስለመግለጽ ፤</u>**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በሂሳብ እና ኦዲት ባለሙያዎች ላይ ከጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ፈቃድ ስረዛ የሚደርስ እርምጃ እንዲወሰድ የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን መጠየቁን፣ ቢሮው ህግን ተከትሎ ጥያቄውን እስካቀረበ ድረስ ማህበራችን ምንም አይነት ቅሬታ የለውም፣ እንደውም ቢሮው ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (AABE) ያቀረበው ጥያቄ ህጋዊና በታክስ አስተዳደር ***ለዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 48 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ)*** በተሰጠው ስልጣን መሰረት በህግ የተሰጠውን ሀላፊነት እንደተወጣ እናምለን።

ሆኖም ግን ከታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች ጉዳዩን በሚዲያ በማሰራጨታቹ <u>በሙያውና በባለሙያዎች ላይ የደረሰውን ሙያዊ ኪሳራ እና በድርጊቱ የተሰማንን ቅሬታ</u> የተሰማንን ቅሬታ እንገልጻለን፦

2.1. በታክስ አስተዳደር ***ለዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 48 ንኡስ አንቀጽ 2/ሀ)*** በግልጽ እንደተቀመጠው ቢሮው ያለው ሀላፊነት ወይም ስልጣን በዚህ ዙሪያ ያለውን ጥያቄ ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (AABE) ማቅረብና ማስወሰን እንጂ፣ ምንም አይነት የህግ አግባብ ሳይሰጣቹ ጉዳዩ ውሳኔ ሳያገኝ በሚዲያ ማሰራጨታቹ ተገቢ ነው ብለን አናምንም፤

2.2. ገና ጥያቄ አቀረባችሁ እንጂ ውሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ ጉዳዩን በሚዲያ ማሰራጨታቹ በሙያውና በሙያተኞች ላይ የስም ማጥፋት እንደፈጸማችሁ ቆጥረነዋል፤ በዚህም ከፍተኛ የሆነ፣ በቀላሉ ሊተካ የማይችል ሙያዊ ኪሳራ አድርሳችሁብናል ብለን እናምናለን፤

2.3. ያቀረባችሁት ጥያቄ በኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (AABE) ወደፊት ተቀባይነት ቢያገኝ እንኳን እንደዚህ አይነት ጉዳዮችን በሚዲያ የማሰራጨት ሀላፊነት በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (AABE) ብቻ ነው፤ በመሆኑም ድርጊቱ እጅግ በጣም አሳዝኖናል፤

2.4. ውሳኔ ባልተሰጠበት ሁኔታ ጉዳዩን በሚዲያ በማሰራጨታቹ፣ ችግሮችም ካሉ ሊሰወር ሲል ተገኝ በተባለው ገቢ፣ በናንተ በኩል በአሰራር ጥፋት እና ግድፈት እንዲሁም አንዳንድ ስነምግባር እና የሂሳብ እውቀት የጎደላቸው ሰራተኞቻቹ እና የስራ ሀላፊዎች፣ በታክስ ከፋዩ ላይና በባለሙያዎች ላይ የሚያደርሱትን ብልሹ አሰራር ለመሸፈን ሲባል ሆነብላችሁ ያደረጋችሁት ሊሆን ይችላል የሚል አመለካከት እንድንይዝ አስችሎናል፤

2.5. ድርጊቱን የፈጸማችሁት የራሳችሁን እና የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድን (AABE) ስም እና ሎጎ ጎን ለጎን በማድረግ ሲሆን፣ ይህም የሚመስለው በጉዳዩ ላይ AABE በጉዳዩ ውሳኔ እንደሰጠበትና ያለቀ ጉዳይ እንደሆነ አድርጋችሁ ነው፣ በመሆኑም ይህ ድርጊታችሁ AABE ያቀረባችሁትን ጥያቄ ገለልተኛ ሆኖ ምርመራውን እንዳይሰራ ከወዲሁ ጫና ለመፍጠር ሊሆን ይችላል የሚል አስተሳሰብ ፈጥሮብናል፤

2.6. ባለሙያው ስለተጠየቀበት ጥያቄ መረጃ ሳይደርሰው፣ ምላሽ ሳይሰጥ፣ ከወዲሁ ጥፋጠኛ እንደሆነ አስመስሎ በማቅረብ ህዝብንና መንግስትን የማሳሳት ተግባር መፈጸማችሁን እንድንገነዘብ አስችሎናል።

2.7. በህገሪቱ ሙያውን እና ባለሙያዎችን የሚወክል፣ የሚቆጣጠርና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የቅጣት ውሳኔ የሚወስድ፣ በህግ ስልጣን ያለው አካል የኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ (AABE) ሆኖ ሳለ፣ ጉዳዩ በ AABE ባልታየበትና ውሳኔ ባልተሰጠበት፣ በቅድመ ኦዲት ተገኘ በተባለ መረጃ ብቻ፣ ያውም በአንድ ወገን ብቻ በቀረበ ማስረጃ፣ ባለሙያው ራሱን መከላከል በማይችልበት፣ ጉዳዩ እንደተፈጸመ እና የመጨረሻ ውሳኔ እንደተሰጠበት በሚያስመስል መልኩ ተሸቀዳድሞ በሚዲያ ማሰራጨት ከበተስተርጃባው ሊደበቁ የተፈለጉ ጉዳዮች እንዳሉ ምልከታ የሚሰጥ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፤

2.8. ድርጊቱ ሁሉንም ባለሙያዎች ያስቆጣና፣ በሙያቸው እንዲያፍሩ፣ በሀገራቸው ተስፋ እንዲቆርጡ የሚያደርግ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፤

2.9. ቢሮው ይህን ውሳኔ ያላገኘ፣ ገና በጥያቄ ደረጃ ያለን ጉዳይ በሚዲያ በማሰራጨት ብቻ ያቆማል ብለን አንጠብቅም፣ እንደውም ጉዳዩን የበጎ ስራ አፈጻጸም ሪፖርት በማድረግ እና ለበላይ አካል በማቅረብ፣ አንዳንድ የናንተ የታክስ ቢሮ ሰራተኞችና የስራ ሀላፊዎች ያሉባቸውን የእውቀት ማነስና የስነምግባር ብሉሽነት፣ ለጊዜውም ቢሆን በመደበቅ ፣ ችግሩን የአንድ ወገን ብቻ እንደሆነ አድርጎ በማሳየት፣ በበላይ አለቆች ዘንድ ተመስጋኝ ለመሆን ያለመ ተግባር ነው ብለን እንድረዳ አስችሎናል፣ ውጤቱ ግን ህዝብን እና መንግስትን ከማሳሳት ይዘላል ብለን አንጠብቅም።

2.10. ይህ ጉዳይ በሚዲያ ከተሰራጨ በኋላ፣ ባለሙያዎች በደምበኞቻቸው፣ በየቅርንጫፉ ባሉ የታክስ ቢሮ ሰራተኞችና ሀላፊዎች፣ ሲከፋም በልጆቻቸውና በቤተሰቦቻቸውም ጭምር ታማኝነትን አጥተው፣ እንደሌባ እንዲታዩ፣ በሀገርና በመንግስት ላይ ክህደት እንደፈጸሙ፣ በሄዱበት ቦታ እንዲሸማቀቁ እና አንገታቸውን እንዲደፉ የሚያደርግ ተግባር እንደሆነ ለመረዳት ችለናል።

በአጠቃላይ ውሳኔ ያላገኘን ጉዳይ፣ ምንም አይነት የህግ አግባብ በሌለበት፣ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ ከግምት ውስጥ ያላስገባ፣ ሀላፊነት የጎደለው ተግባር፣ በባለሙያው ላይ ከፍተኛ የሆነ የስነልቦና ጫና ያደረሰ፣ በማህበራችን ከ 50 አመት በላይ በሆነ ጉዞ ደርሶብን የማያውቅ በሙያችን ላይ የደረሰ ከፍተኛ ሙያዊ ኪሳራ ሆኖ ተመዝግቧል።

3. **<u>ቢሮው በሚዲያ ያስተላለፈውን መልእክት ማስተባበያ እንዲሰጥበት እና መልእክቱን እንዲሰርዝ ስለመጠየቅ።</u>**

ምንም እንኳን ጉዳዩ በሚዲያ በመሰራጨቱ በሙያችን እና በባለሙያው ላይ የደረሰውን ችግር ባይቀርፈውም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የእርምት እርምጃዎች እንዲወሰዱ በታላቅ ትህትና እንጠይቃለን፡

3.1. ጉዳዩ ውሳኔ ያለገኘና በሂደት ያለ መሆኑ እና ቀድሞውንም በሚዲያ መሰራጨቱ አግባብ እንዳልነበር የሚገልጽ መልእክት ጉዳዩ በተላለፈባቸው ሚዲያዎች የማስተባበያ ዘገባ እንዲዘገብልን፤

3.2. ጉዳዩ ከየትኛው የሚዲያ መረጃ ማጠራቀሚያ እና ቢሮው ከሚቆጣጠራቸው የሶሻል ሚዲያ ገጾች እንዲሰረዝልን፤

3.3. ወደፊት ጉዳዩ ውሳኔ አግኝቶ በሚዲያ ከመሰራጨቱ በፊት፣ ባለሙያው እራሱን ከጉዳዩ ነጻ መሆኑን ለማስረዳት የሚችልበትን ህጋዊ መንገዶች አሟጦ ሳይጠቀም የታክስ መስሪያቤቱ ሰራተኞችና የስራ ሀላፊዎች መሰል ድርጊቶችን ከማድረግ እንዲታቀቡ ጥብቅ ማሳሰቢያ እንዲሰጥልን፤

3.4. በሸገር ኤፍ ኤም ዘገባ ላይ እንደቀረበው ጥፋተኛ ናቸው የተባሉትን ነገርግን ጥፋተኛ መሆናቸው ገና ያልተረጋገጡትን ባለሙያዎች ስም ዝርዝር በየቅርንጫፉ እንደሚለጠፍ ተዘግቧል፣ ነገር ግን ቢሮው በሚመለከተው አካል ውሳኔ እስከሚተላለፍ ድረስ ከዚህ ድርጊቱ እንዲታቀብ፤

3.5. በነዚህና በሌች ከታክስ ስርአቱ ጋር ለሚስተዋሉ ችግሮች የጋራ መፍትሄ ለማበጀት ፣ ከማህበራችን የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጋር በቅርብ ቀን አስችኳይ የምክክር እና የውይይት መድረክ እንዲዘጋጅልን እንጠይቃለን።

ከሠላምታ ጋር!

የኢትዮጲያ የሂሳብ አዋቂዎችና አዲተሮች ማህበር

የዳይሬክተሮች ቦርድ

ዮሐንስ ንጋቱ (FCCA)
የኢ.ሂ.አ.አ.ማ ፕሬዝዳንት
Yohannes Negatu (FCCA)
EPAAA President

<u>ግልባጭ፡</u>

- **ለኢትዮጲያ የሂሳብ አያያዝና አዲት ቦርድ (AABE)**
- **ለገቢዎች ሚኒስቴር**
- **ለፋይናንስ ሚኒስቴር**
- **ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
- **ለሁሉም ሚዲያዎች**